# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሰፕቴምበር 21-30 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከኦክቶበር 1-10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2021
አዲስ አበባ

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ........ 1

ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 4

እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5

እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 6

በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው ........ 7

የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8


# እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት በመዳከማቸዉ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ከአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም አብዛኛዉ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ምዕራብና ማካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ የሲዳማ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የአፋር ደቡባዊ ክፍል፣ የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ጥቂት የምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በአርሲና ባሌ፣ በሁሉም የሸዋና ወለጋ፣ በኢሉባቦርና ጅማ ዞኖች፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በአሶሳ፣ በጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በቤንች ማጂ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ እና በሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ25-137 ሚ.ሜ. የሚደርሰ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የዘነበ ሲሆን፣ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከ5-25 ሚሜ የሚደርስ ከሶስት ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምስዘራቅ ጎጃም፣ በወሎ ዞኖች፣ በሰሜን ሸዋ(03)፣ በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በኢሉባቦርና ጅማ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ በአርሲና ባሌ፣ በጉጂና ቦረና፣ በአብዛኛዎቹ የአፋር ክልል ዞኖች፣ ከጥቂት የፋፈንና ደገሃቡር ዞኖች በስተቀር በሁሉም የሱማሌ ክልል ዞኖች፣ በጋምቤላና ሲዳማ ክልል ዞኖች፣ በሸካ፣ በከፋ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ እና በሀዲያ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት በመዳከማቸዉ ዝናቡ በመጠንም ሆን በስርጭት ረገድ ከአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአመዛኙ እርጥበታማ ሁኔታ ተጠናክሮ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም በምዕራብ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ከማቅረብ አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ እንዲሁም እርጥበቱ ከሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ቀንሶ የተስተዋለ ቢሆንም በምስራቅ ኢትዮጵያ እና ጥቂት የአፋር ደቡባዊ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ በማግኘታቸው ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተሻለ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበረ:: በተመሳሳይ ሁኔታ ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ ለነበሩትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡባዊ ክፍል በመጠኑም ቢሆን የእርጥበት ሁኔታቸው እንደተሻሻለ የተሰበሰቡና የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በአካባቢዎቹ የነበረውን ደረቅ ሁኔታ ከማስታገስና በደቡብ የሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርና የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና እንደነበረው ነው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-30 ሴፕቴምበር 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከመስተዋሉም በተጨማሪ ወደ ምስራቃዊና ደቡባዊ ተፋሰሶች በመስፋፋት የተሻለ ገፅታ ነበረው። ይህንን ተከትሎ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የገናሌዳዋ ምዕራባዊ አጋማሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ በጥቂት ተከዜ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 21 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ቀደም ብሎ የጀመረው የክረምት ወቅት ዝናብ በምዕራብ አጋማሽ የሚቀጥል ሲሆን፣ በተጨማሪም ወደ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ሊስፋፋ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፣ አልፎ አልፎም ከሚኖረው እርጥበታማ የአየር ሁኔታ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ አርሲና ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጉጂ ዞኖች፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ምዕራብ ጎጃምና ምስራቅ፣ ሰሜን ሸዋ እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ ከደቡብ ኦሞ ዞን በስተቀር ሁሉም የክልሉ ዞኖች እንዲሁም የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ጠንካራ ደመናዎች በሰሜንና በደቡብ ወሎ እንዲሁም በደቡብ አፋር ዞን 3 እና 5 ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ ከሶማሌ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ አዲስ አባባ እንዲሁም ጋምቤላ አነስተኛ ዝናብ እንደሚያገኙ የጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ገጽታ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የመኸር ሰብል አምራች በሆኑትም ሆነ የክረምት

ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የእርጥበት ሁኔታው ከቀደመው አንጻር ሲታይ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ጥንካሬ ይዘው ሊቀጥሉ እንደሚችሉና በተለይም ዝናቡ በምዕራባዊው አጋማሽ እና በተጨማሪም ወደ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና ስራ እንቅስቃሴዎች ገንቢ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል። በተጨማሪም ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱ እንዲሁም በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም በዚህ ጊዜ የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት ወቅታዊ እርጥበት ማግኘት በሚጀምሩት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደጋማ አካባቢ ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በስፋት በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደሚኖረው ይታመናል። በሌላ በኩል ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በሌላም በኩል በዚህ ጊዜ በመደበኛ ሁኔታ የሰብል ስብሰባ በሚካሄድባቸው በሰሜናዊ አጋማሽም ሆነ በአንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ሊኖር የሚችለው ደረቅ ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ እንደሚሆን ነው፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታል። ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤና ስምጥሸለቆ፣ የደቡባዊና የምዕራባዊ አጋማሽ አባይ፣ የላይኛው አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌና በአብዛኛው የገናሌዳዋ ተፋሰሶች እርጥበታማ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአብዛኛው አዋሽ፣ ምስራቃዊ አባይ፣ የታችኛው ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ፣ የታችኛው ባሮአኮቦ እና የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል።